# Thomas Jefferson Middle School

## *የ IBMYP የጃንዋሪ የዜና መጽሄት*

*ራሳችንን፣ የወደፊት ሕይወታችንን እና ዓለማችንን ለማወቅ እና ለማሻሻል አብሮ መማር።*

### የወሩ የተማሪ መገለጫ ባህሪ: አሰላሳይ



ሁሉም ተማሪዎቻችን **አሰላሳዮች እንዲሆኑ እንፈልጋለን።** ለመማር ቁልፍ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ በመደበኛነት የተማሩትን ጉዳይ ማሰላሰል ነው። በ Jefferson ተማሪዎቻችን አብዛኛውን ጊዜ በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ይህን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። መምህራን እያንዳንዱን የምእራፍ ክፍል ከማስተማራቸው በፊት፣ በማስተማር ላይ ሳሉ እና ካስተማሩ በኋላ እንዲያሰላስሉ ይጠየቃሉ። በተጨማሪም በግልም ሆነ በአካዳሚያዊ ሕይወታችን ውስጥ፣ ነገሮችን የምናሰላስል መሆናችን የተሻልን እና የበለጠ ተንከባካቢ ሰው ለመሆን ይረዳናል። በተማሪዎቻችን የተመረጡ ምርጥ አሰላሳይ ተማሪዎቻችን የሚከተሉት ናቸው: **Dolphins - Landan Gallardo፣ Dragons-Sophia Voulgaris፣ Eagles-Ryan Phillips፣ Gators-Anthony Vergara፣ Monarch-Olivia Bartrum፣ Owls-Maya Yilmaz፣ Penguins-Devyn Carlson፣ Phoenix-Amelia Sahm** እና **Stingrays-Jihan Matthews** ናቸው። ምንጭ: JeffersonIBMYP

### የተፃፈ ሥርዓተ-ትምህርት

የቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ (ELA) ክፍሎች አዲሱን ዓመት በብዙ ኢ-ልቦለድ ንባብና ጽሁፍ በመጀመር ላይ ናቸው። በ MYP 1ኛ አመት፣ ELA ተማሪዎች በማግባባት ጽሁፍ አንድ የምእራፍ ክፍል ሲያጠናቅቁ ቆይተዋል። በተለይም፣ ተማሪዎች በተመረጡ አጫጭር ታሪኮች ውስጥ እንዴት የገፀ ባህሪያትን መገለጫ ባህሪያት ሀተታ እንደሚያጠናቅሩ እና ሀተታቸውን ለመደገፍ ከእነዚህ ታሪኮች ማስረጃዎችን በመጠቀም - እንዴት አሳማኝ ፅሁፎችን እንደሚጽፉ ተምረዋል። በንባብ 6፣ ተማሪዎች ፈጠራን፣ ውዝግብን፣ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን እና ጽናትን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ጽንሰ-ሐሳቦች ለመመርመር የተለያዩ ኢ-ልቦለድ ጽሑፎችን እያነበቡ ነው። በተጨማሪም ስለ ደራሲ ዓላማ፣ አድልዎ እና የአደረጃጀት ቅጦች እየተማሩ ነው።

### ረቂቅ የማካተት ፖሊሲ



በድረ-ገጽ ላይ ረቂቅ የማካተት ፖሊሲ አለን። የአካዳሚያዊ ቅንነት ፖሊሲያችን ይፈልግ የነበረው የተወሰኑ ጥቃቅን ለውጦችን ብቻ ሲሆን፣ የቋንቋ ፖሊሲያችን ሙሉ በሙሉ መከለስ ይፈልግ ነበር፣ እንዲሁም የማካተት ፖሊሲያችን ግን በሁለቱ መሃል ላይ ያርፋል። ከማካተት ፖሊሲያችን ጀርባ ያሉትን ፍልስፍና እና መርሆዎችን በጣም ግልጽ ያደረግን ሲሆን የመለያ ክፍሉን በአብዛኛው ተመሳሳይ አድርገን ትተነዋል። በመቀጠልም አካታች ትምህርት እንዴት ለሁሉም እንዲሰራ እንደምናደርግ ሁሉም እንዲመለከት የት-ብብር ክፍልን እንጨምራለን። በ Jefferson እያንዳንዱ መምህር የሁሉም ተማሪዎች አስተማሪ ነው። መምህራን አካታች ስትራቴጂዎችን በመጠቀም አብረው እቅድ ማውጣት ያስፈልጋቸዋል። አሁን በምእራፍ ክፍል እቅድ አዘጋጆችን ላይ የቲሲስ ምርምርን መሰረት ያደረገ የማስተማር ዘዴን አካትተናል። በመጨረሻም፣ በደረጃ አሰጣጥ ላይ ጥራት እና እኩልነትን ለማረጋገጥ የመመዘኛ ክፍልን አክለናል። ማንኛውንም ግብረመልስ በደስታ እንቀበላለን። ምንጭ: pixbay.com

### የ MYP መማሪያ ክፍሎች እና እውነተኛ ምዘናዎች



የቋንቋ እና የስነ-ጽሑፍ ትምህርቶች የአክቲቪዝም ክፍላቸውን እየዳሰሱ ነው። ከተለምዶአዊ የሶቅራጥስ ሴሚናሮች ትንሽ ለየት ባለ መልኩ፣ ELA 7 ተማሪዎች Washington-Lee ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስሙን መቀየር አለበት ወይም የለበትም የሚለውን አስመልክቶ የሚደረገውን ውይይት ለማቀድ እና ለመምራት ከአጋሮች ጋር እንዲሰሩ አድርጓል። ተማሪዎች አወዛጋቢ በሆነ ርዕስ ጉዳይ ሀሳብ ሰፊ መሆንን በሚገባ ተለማምደዋል። እና Washington-Lee ስሙን መቀየር ወይም አለመቀየሩን በተመለከተ በመካከላቸው አለመግባባት ቢኖርም አንዳቸው ሌላኛቸውን አድምጠዋል። በመጨረሻም፣ ተማሪዎች በአፈጻጸማቸው ላይ አሰላስለዋል - በእውነትም የዜግነት እና የመግባቢያ ክህሎቶችን ለማስተማር ግሩም መንገድ ነው። ፎቶ በ Mr. Malinosky

### የማኅበረሰብ ፕሮጀክት ማመልከቻዎች ለድርጊት



ጃንዋሪ በአብዛኛው ለአገልግሎት ሰጪ ድርጅት በጣም አስቸጋሪው ወር ነው። ከበዓል ቀናት በኋላ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ብዙም የሚሰጡት ነገር የላቸውም። የ Jefferson ተማሪዎች ግን እያጠናከሩ ናቸው። በተለይም በማኅበረሰብ ፕሮጀክቶች፣ ተማሪዎች በብስክሌት ልገሳ፣ ለቤት አልባዎች የምግብ ማሰባሰቢያዎች፣ በባዶ ግድግዳዎች ላይ ስእሎችን መሳል፣ የኮራል ቀለም መልቀቅን ለማቆም ገንዘቤን ማሳደግ፣ የሌሊት ወፎችን የሚገጥሙ አደጋዎች እና ሌሎች ብዙ ብዙ ተጨማሪ ርእሶች በማቀድ ላይ ናቸው። ቁልፉ ጉዳይ ተማሪዎች የትምህርታቸው መሪ መሆናቸው ነው። አሁን ሁሉም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የድርጊት እቅድ ማውጣት አለባቸው። ምንጭ: pixbay.com

### የ Jefferson የሳይንስ ፌስቲቫል




የዓለም የወደፊት እጣ ፈንታ በ Jefferson ተማሪዎች እጅ የሚሆን ከሆነ፣ ዓለም የተሻለች ቦታ እንደምትሆን ምንም ጥርጥር የለውም። ተማሪዎቻችን ካፌይን (በአፍ ሙሉ በአንድ ትንፋሽ መዋጥ) በአይጥ ላይ ከሚያደርሰው የጤና ውጤቶች እስከ ፎስፈረስ እና ናይትሮጅን ይዘት ያላቸው የአካባቢ የውሃ ምንጮች ጥራት ድረስ ያሉ የሳይንስ ፌስቲቫል ምርቶችን ፈጥረዋል። ተማሪዎች፣ የታሰበባቸው መላምቶችን መፍጠር፣ ነጻ ተለዋዋጮችን መምረጥ እና ጥገኛ ተለዋዋጮችን መለካት እንደሚችሉ አሳይተዋል። ተማሪዎች ለዳኞቹ (ለመምህራን) ወጣት ሳይንቲስቶች እና ጥሩ የሃሳብ ልውውጥ አድራጊዎችን እያበቀሉ መሆናቸውን አሳይተዋል። ፎቶ በ Mr. Malinosky።

### National Geography Bee (አመታዊ የጀግራፊ ውድድር)



Jefferson የ National Geography Bee አመታዊ የጀግራፊ ውድድርን በጃንዋሪ 18 ላይ አካሂዷል። የ TJMS ሻምፒዮን ለመሆን ሰባት የመጨረሻ ተወዳዳሪዎች ተወዳድረዋል። ተማሪዎች ከደቡብ አሜሪካ ጃግዋሮች እስከ ሩሲያ ሃይቆች የሚያካልሉ ጥያቄዎችን በመመለስ አስደማሚ ዓለማቀፋዊ ግንዛቤያቸውን አሳይተዋል። ከ 40 ደቂቃ ጥያቄዎች በኋላ፣ Sassan Fiske ውድድሩን አሸንፏል። አሁን Sassan በስቴት ሻምፒዮና ላይ ይወዳደራል። ምንጭ: ፎቶ በ Mr. Malinosky።

### መጪ ቀናት/የአገልግሎት ፍላጎቶች

- ዘወትር ረቡዕ የኮሙኒቲ ፕሮጀክት እገዛ በቤተ መፃህፍት ውስጥ
- ዘወትር ማክሰኞ 5pm ላይ በ Phoenix Bikes በብስክሌቶች ጥገና ላይ በበጎ ፈቃድ መካፈል፣ 909 S. Dinwiddie St (ሙሉ ዝርዝሩን እዚህ ያግኙ)
- ዘወትር ረቡዕ በ 6:30pm በ AFAC የዶሮ ስጋን በመጠቅለል በበጎ ፈቃድ መካፈል፣ 2708 S. Nelson St, (ሙሉ ዝርዝሩን እዚህ ያግኙ)
- የምግብ አውቶብሱን ግንኙነት ለማስተካከል Mr. Malinoskyን ያናግሩ
- የአገልግሎት ትምህርት የቀን መቁጠሪያ እዚህ ይገኛል